አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

# አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ

# ADDIS NEGARI GAZETA

## OF THE CITY GOVERNMENT OF ADDIS ABABA

አንደኛ ዓመት ቁጥር ፭
አዲስ አበባ ፪ሺ ዓ.ም.

በአዲስ አበባ ከተማ
ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

First year No. 5
ADDIS ABABA 2008

**ማውጫ**

የከተማው አስተዳደር አካላት የአስተዳደሩን ቤቶች የማስተላለፍ ኃላፊነታቸውንና አፈፃፀሙን ለመወሰን የወጣው አዋጅ ቁጥር ፲፱/፲፱፻፺፯ እንደገና ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር ፭/፪ሺ.ዓ.ም

**CONTENTS**

A PROCLAMATION TO RE-AMEND THE PROCLAMATION TO PROVIDE FOR THE RESPONSIBILITIES OF THE CITY GOVERNMENT ORGANS IN THE TRANSFER OF THE CITY GOVERNMENT HOUSES AND ITS EXECUTION PROCLAMATION NO.19/2005

**አዋጅ ቁጥር ፭/፪ሺ.ህ**

**የከተማው አስተዳደር አካላት የአስተዳደሩን ቤቶች የማስተላለፍ ኃላፊነታቸውንና አፈፃፀሙን ለመወሰን የወጣው አዋጅ ቁጥር ፲፱/፲፱፻፺፯ እንደገና ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር ፭/፪ሺ.ዓ.ም**

የአስተዳደሩን የጋራ ህንጻ ቤቶች በማስተላለፍ ሂደት የተገኙ ጠቃሚ ተሞክሮዎችንና ያጋጠሙ ችግሮችን ከግምት ውስጥ በማስገባት የተሻለ የቤት ማስተላለፍ አፈጻጸም እንዲኖር ማድረግ በማስፈለጉ፣

ይህንኑ ለመፈፀም የከተማው አስተዳደር አካላት የአስተዳደሩን ቤቶች የማስተላለፍ ኃላፊነታቸውንና አፈፃፀሙን ለመወሰን የወጣውን አዋጅ ቁጥር ፲፱/፲፱፻፺፯ /እንደተሻሻለ/ እንደገና ማሻሻል በማስፈለጉ፣

የአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት በተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር ፫፻፷፩/፲፱፻፺፭ (እንደተሻሻለ) አንቀጽ ፲፬/፩/ሀ/ በተደነገገው መሠረት ይህንን አዋጅ አውጥቷል ::

**፩. አጭር ርዕስ**

«ይህ አዋጅ የከተማው አስተዳደር አካላት የአስተዳደሩን ቤቶች የማስተላለፍ ኃላፊነታቸውንና አፈፃፀሙን ለመወሰን የወጣው አዋጅ ቁጥር ፲፱/፲፱፻፺፯ እንደገና ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር ፭/፪ሺ.ዓ.ዓ.ም» ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

**Proclamation No 5/2008**

**A Proclamation to Re-amend the proclamation to provide for the Responsibilities of the city Government Organs in the Transfer of the City Government Houses and its execution Proclamation No.5/2008**

**WHEREAS,** it is found necessary to have better execution of transfer of houses by taking in to account the best practices and problems encountered in the process of transferring condominiums of the City Government.

**WHEREAS,** it is found necessary to re-amend the proclamation to provide for the responsibility of the City Government organs in the transfer of the City Government house and its execution proclamation No. 19/2005.

**NOW, THEREORE,** in accordance with Article 14(1) (a) of the Revised Charter of Addis Ababa City Government proclamation No 361/2003, it is hereby proclaimed as follows,

1. ***Short Title***

This proclamation may be cited as "A proclamation to Re-amend A proclamation No. 19/2005 the proclamation to provide for the Responsibilities of the City Government Organs in the Transfer of the City Government Houses and its Execution, No 5/2008.

## ፪. ማሻሻያ

የከተማው አስተዳደር አካላት የአስተዳደሩን ቤቶች የማስተላለፍ ኃላፊነታቸውንና አፈፃፀሙን ለመወሰን የወጣ አዋጅ ቁጥር ፲፱/፲፱፻፺፯ (እንደተሻሻለ) እንደሚከተለው እንደገና ተሻሽሏል፡፡

፩ የአዋጁ አንቀጽ ፮ ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ ፮ ተተክቷል፡-

### ፮ የቅድሚያ አወሳሰን

፩. ከክፍለ ከተማ የመሬት ልማትና አስተዳደር ጽህፈት ቤት በሚገኘው መረጃ መነሻ በከተማው ካቢኔ በሚወሰነው መሠረት እስካሁን በቤት ልማት ፕሮግራም አፈጻጸም ተነስተው በመጠለያ ውስጥ ላሉና በቀጣይ በቤት ልማት ምክንያትም ሆነ በከተማው የመሃል አካባቢ በሚከናወኑ የመልሶ ማልማት ፕሮጀክቶች ምክንያት በፈቃዳቸው ለሚነሱ የከተማው ነዋሪዎች የተወሰነ የቤት ድርሻ በልዩ ሁኔታ ተይዞላቸው ቤቶችን የመግዛት የቅድሚያ መብት ሊያገኙ ይችላሉ፡፡ ሆኖም በዚህ የቅድሚያ መብት ተጠቃሚ የሚሆኑት የመጠለያ ነዋሪዎችና ሌሎች ተነሺዎች በተነሱበት ቀበሌ የግል ቤት ባለቤቶች፣ የግል ቦታ ባለይዞታዎች ወይም የመንግስት ቤት ከአከራዩ መስሪያ ቤት የተከራዩ የከተማው ነዋሪዎች ወይም አብረዋቸው የሚኖሩ ህጋዊ ወራሾቻቸው ብቻ ይሆናሉ፡፡

፪ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ለሽያጭ የቀረቡት መኖሪያ ቤቶች በአንቀጽ ፭ ንዑስ አንቀጽ ፫ መሠረት ለተመዘገቡት ቤት ፈላጊዎች በሽያጭ የሚተላለፉት በዕጣ ብቻ ይሆናል፡፡

፫ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፭ ንዑስ አንቀጽ (፫) መሠረት በቤት ፈላጊነት የተመዘገቡ እስከሆኑ ድረስ ቢያንስ ፴ ፐርሰንት ሴቶች በእያንዳንዱ የዕጣ ማውጣት ሥርዓት ተካትተው ቤት የመግዛት የቅድሚያ መብት ተጠቃሚዎች ይሆናሉ፡፡

፬ የእንቅስቃሴ አካል ጉዳተኛ የሆነ ቤት ፈላጊ ቤት ለመግዛት ዕጣ እስከወጣለት ድረስ ምርጫው እንደተጠበቀ ሆኖ ተደራሽ በሆነው የሕንጻው ወለል ላይ የሚገኝ ቤት የመግዛት ቅድሚያ ያገኛል፡፡ ይህ መብት ለቤተሰብ አባላት አይተላለፍም፡፡ ማንኛውም ቤት ፈላጊ ይህንን የቅድሚያ መብት መቃወም አይችልም፡፡

፪. በአዋጅ አንቀጽ ፱ ሥር በአዋጅ ቁጥር ፳፱/ ፲፱፻፺፱ ከተጨመረው ንዑስ አንቀጽ ፬ ቀጥሎ አንቀፅ ፭ ተጨምሯል፡-

፬ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እስከ (፫) የተደነገገው ቢኖርም የከተማው ካቢኔ ከባንክ ጋር በሚደረግ ስምምነት መሠረት በሌላ መልክ እንዲፈጸም ሊወስን ይችላል፡፡

## 2. Amendment

The proclamation to provide for the Responsibilities of the city Government organs in the Transfer of the City Government Houses and its execution No 19/2005 /As Amended/ is here by amended as follows.

1. **Article 6 of the proclamation is deleted and substituted by the following new Article 6.**

### 6. Setting priority

1. Residents of the City who are so far evacuated and living in a temporary camp because of execution of the housing development program and those evacuated voluntarily in the future due to the housing development as well as the renewal projects to be effected in the inner City, shall be entitled to a special arrangement and prior right of purchasing houses based on the decision of Cabinet of the City on the basis of the information found with the sub-city office of Land Development and Administration. However one living in a temporary Camp or evacuated in order to be entitled to the prior right of purchasing a house shall be resident of the City or lawful successor who is owner of private house, possessor of piece of land, or lessee of government house from the appropriate office within the kebele from which he is evacuated.

2. Notwithstanding the provisions of sub-article (1) of this Article, the houses ready for sale shall be transferred on sale to persons registered in accordance with Article 5(3) only on lot basis.

3. Women registered according to Article 5(3) of this proclamation shall be included in each session of drawing lot at least 30% and entitled to prior right of purchasing house.

4. A person disabled as regards movement and winner of lot as a house seeker, without prejudice to his choice, shall be entitled to prior right to buy a house on the floor accessible. This right shall not be transferred to family members. No house seeker may present objection against this prior right.

2) The following new sub-article (5) is added under Article 9 following sub-Article 9 (4) added by Proclamation no 29/2007

(4) with respect to sub article 1-3 of this Article with the agreement from bank the city cabinet may fir by delusion the implantation to dare in a thereby

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

# አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ

# ADDIS NEGARI GAZETA

## OF THE CITY GOVERNMENT OF ADDIS ABABA

አንደኛ ዓመት ቁጥር ፯
አዲስ አበባ መስከረም ፳፰ ቀን ፪ሺ፩ ዓ.ም.

በአዲስ አበባ ከተማ
ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

1st Year No. 7
ADDIS ABABA October 7, 2008


## ማውጫ


የከተማው አስተዳደር አካላት የአስተዳደሩን ቤቶች ማስተላለፍ አዋጅ..........................................ገጽ ፩


## CONTENT


City Government Grievance Organs Transfer of the City Government Houses Proclamation ............ Page 1


**አዋጅ ቁጥር ፯/፪ሺ፩**

**የከተማው አስተዳደር አካላት የአስተዳደሩን ቤቶች የማስተላለፍ ኃላፊነታቸውንና አፈፃፀሙን ለመወሰን የወጣ አዋጅ ቁጥር ፲፱/፲፱፻፺፯ እንደገና ማሻሻያ አዋጅ**

የከተማው አስተዳደር አካላት የአስተዳደሩን ቤቶች የማስተላለፍ ኃላፊነትና አፈፃፀሙን ለመወሰን የወጣውን አዋጅ ቁጥር ፲፱/፲፱፻፺፯ (እንደተሻሻለ) በልዩ ሁኔታ ታይተው ቤት ማግኘት የሚገባቸው ተጠቃሚዎችን ጥያቄ ከዕጣ ውጭ ማስተናገድ የሚያስችል አሰራርን ባካተተ መልኩ እንደገና ማሻሻል በማስፈለጉ፣

የአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት በተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር ፫፻፷፩/፲፱፻፺፭ አንቀጽ ፲፬/፩/ሀ መሠረት ይህንን አዋጅ አውጥቷል።

፩. **አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ ‹‹የከተማው አስተዳደር አካላት የአስተዳደሩን ቤቶች የማስተላለፍ ኃላፊነታቸውንና አፈፃፀሙን ለመወሰን የወጣ አዋጅ ቁጥር ፲፱/፲፱፻፺፯ እንደገና (እንደተሻሻለ) ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር ፯/፪ሺ፩ ዓ.ም.›› ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

**Proclamation No. 7/2008**

**A Proclamation to provide for the Responsibilities of the City Government Houses and its Execution Proclamation No. 19/2005 Re-amendment Proclamation**

**WHEREAS,** it has become necessary to re-amend the proclamation to provide for the Responsibilities of the City Government Organs in the Transfer of the City Government House and its Execution Proclamation No/ 19/2005 (as amended) in order to develop a system in which home seekers exceptionally acquire houses without casting lot;

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 14(1) a of the Addis Ababa City Government Revised Charter Proclamation No. 361/2003, the City Council hereby Proclaims as follows;

1. ***Short Title***

This Proclamation may be cited as "A Proclamation to Provide for the Responsibilities of the City Government Organs in the Transfer of the City Government Houses and its Execution Proclamation No. 19/2005 re-amendment Proclamation No. 7/2008".


ያንዱ ዋጋ
Unit Price 4.90

አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ ፪ሺ፬፻፵፭
Addis Negari Gazeta P.O.Box 2445

## ፪. ማሻሻያ

የከተማው አስተዳደር አካላት የአስተዳደሩን ቤቶች የማስተላለፍ ኃላፊነታቸውንና አፈፃፀሙን ለመወሰን የወጣ አዋጅ ቁጥር ፲፱/፲፱፻፺፯ (እንደተሻሻለው) እንደሚከተለው በድጋሚ ተሻሽሏል፡፡

በአዋጁ አንቀጽ ፮ ሥር የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ /፭/ ተጨምሯል፡፡

፭. በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ /፩/ እስከ /፬/ የተደነገገው ቢኖርም፣ የከተማው ካቢኔ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው የቤት ፈላጊዎች ከዕጣ ውጭ በልዩ ሁኔታ ሊስተናገዱ የሚችሉበትን ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡

## ፫. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ ከመስከረም ፳፯ ቀን ፪ሺ፩ ዓ.ም. ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ**
**መስከረም ፳፯ ቀን ፪ሺ፩ ዓ.ም.**

**ኩማ ደመቅሳ**
**የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ**

## 2. *Amendment*

The Proclamation to provide for the Responsibilities of the City Government Organs in the Transfer of the City Government Houses and its Execution Proclamation No. 19/2005 (as amended) is further amended as follows:-

The following new sub-article (5) is added under Article 6 of the Proclamation.

5. Notwithstanding the provisions of sub-Article (1)-(4) of this Article the City Cabinet where it finds necessary may issue regulation to provide for home seekers exceptionally acquire houses without casting lot.

## 3. *Effective Date*

This Proclamation shall enter into force as of the 7th day of October, 2008.

**Done at Addis Ababa**
**This 7th day of October, 2008**

**Kuma Demeksa**
**Mayor of Addis Ababa City**

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ